**የኢትዮጵያ ዘውድ ምክርቤት**

**THE CROWN COUNCIL OF ETHIOPIA**

His Imperial Highness Prince Ermias Sahle-Selassie Haile-Selassie
President


# የልዑል ኤርሚያስ ሣህለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ መልእክት ለኢትዮጵያ አዲስ ዓመት በዓል ፳፻፲፩ ዘመነ ሉቃስ ወንጌላዊ።

በዓለም ዙርያ ለምትገኙ ክቡራን እና ክቡራት የውድ ሀገራችን ኢትዮጵያ ልጆች በሙሉ እንኳን ከ፳፻፲ ዘመነ ማርቆስ ወደ ፳፻፲፩ ዘመነ ሉቃስ አሸጋገረን። እንደ አምናው በዘንድሮም ዘመን መለወጫን በምናከብርበት ጊዜ ኢትዮጵያ እና ወገኖቻችን ኢትዮጵያውያን የምንመኛቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ዘመን በዘመን ሲተካ ወደኋላ ስንመለከት በአለፈው ዓመት በስኬት የፈጸምናቸው ድርጊቶች ሊያስደስቱንና ያልተሳኩልንንም ስናስብ ትምህርት እንዲሆኑን ይገባል። ያለፍናቸው የደስታ እና የሐዘን፥ የስራ እና የእረፍት፥ የምኞት እና የስኬት፥ ግዜዎችን እያስተዋልን ፈጣሪ አምላክን ማመስገን ይገባል። የእንቁጣጣሽ በዓል መሰረቱ ታላቋ ማከዳ ንግሥተ ሳባ ከእየሩሳሌም በተመለሰችበት ግዜ መሳፍንቶቿ “እንኳን በደህና ተመለሽ” ለማለት የእንቁ እና የከበሩ ጌጣጌጥ በስጦታ ስለ ሰጥዋት ነው። ይህ የዘመን መለወጫ በዓል እና የዓመታት፥ የወራት፥ የቀናት፥ የሰዓት፥ አቆጣጠራችን ከጥንት አባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የሚያኮራ ልዩ ባሕላችን ነው። የኢትዮጵያዊነት ልዩ ኩራታችን ነው። ለዚህም ሁሉ የሚያኮራን እና ስማችንን ለሚያስጠራ ልዩ የሆነ የአገር ባሕል እና ሥርዓት አባቶቻችንና እናቶቻችንን ከሁሉም በላይ ፈጣሪን ማመስግን ተገቢ ነው።

ዘመን ሲለዋጥ ያለፈውን በማጤን እና አምላክን በማመስገን፥ የሚመጣውንም በተስፋ እና በጸሎት መቀበል የቆየ ልማዳችን ነው። ከሁሉም በላይ በዚህ በአዲሱ ዓመት ለአገራችን እና ለሕዝባችን ሰላምን እንዲያወርድልን እግዚአብሔርን መለመን ተገቢ ነው። ጦርነት መከፋፈል እና ችግር እጅ ለ እጅ ተያይዘው በኢትዮጵያ ምድር ለበርካታ ዘመናት እምባ እንድናፈስ እና በስደት እንድንበተን አድርጎናል። ይህ እንዲቆም ሰላሙን ፍቅሩን አንድነቱን እና በረከቱን ፈጣሪ እንዲመልስልን መለመን ይገባናል። የዓለም ሰላም በደፈረሰበት እና የኑሮ ውድነት ባየለበት በዚህ አስቸጋሪ ግዜ ከኛ በባሰ ሁነታ ላይ ላሉ ሰዎች በቻሉት መጠን መርዳት ሀለዚያም በጸሎት እና በሐሳብ መደገፍ የሁላችንም ተግባር መሆን ይገባዋል።

ይህ አዲስ ዓመት ለአገራችን ለኢትዮጵያ እና ለልጆቿ እንዲሁም ለመላው ዓለም የሰላም የጤንነት የመታደስ ያድርግልን። ዘመነ ሉቃስ ፳፻፲፩ ዓመተ ምህረትን ልዑል እግዚአብሔር ይባርክልን ለዓመት ዓመት ያድርሰን።